ሕዝብ ማለት "ክራሲ" አገዛዝ ከሚመሩ ሁለት ቃላት የቀመረው ይህ ዘዴ ወይም መሣሪያ መንግሥት ሕዝብን ለማስተዳደርና የፖለቲካውን ሥርዓት ሕጋዊ ለማድረግ የሚጠቀሙበት ነው።

## የዲሞክራሲ ዓይነቶች ስንት ናቸው?

በተለያዩ አገሮች የተለያዩ ዲሞክራሲዎች አሉ። እነዚህም በአምስት ክፍሎች ሊመደቡ ይችላሉ።

1. አውቶክራሲ / Autocracy/ በአንድ አንባገነን የሚመራ ሥርዓት ወይም የአንድ ሰው ዲሞክራሲ ማለት ነው። ይህም ብዙ ጊዜ ውሣኔ የሚሰጠው በአንድ ሰው ብቻ ነው።
2. ኦልጋርኪ/Oligarchy/ የዚህ ዓይነቱ ዲሞክራሲ በጥቂት በጥቅም በተሳሰሩ ሰዎች የሚመራና ብዙውን ጊዜ ውሣኝ አካላት ጥቂቶች የሚሆኑበት መስተዳድር ነው።
3. ዲሞክራሲ /Democracy/ ሲተነተን ዲሞ ሕዝብ ሲሆን ክራሲ ማለት የሕዝብ መስተዳደር ማለት ነው።
4. የስምምነት ዲሞክራሲ /Consensus/ ይህ ከፍተኛ የዲሞክራሲ ብስለት በዘለቀበት አገር የሚደረስበት የዲሞክራሲ የፖለቲካ ባህል ነው።
5. ልምድ /Habit / የዚህ ዓይነቱ የዲሞክራሲ ባህል ከሕዝቡ ጋር ተዋህዶ ውሣኔዎችም ሆኑ ሌሎቹ አፈጻጸሞች ዘዴውን በዕለት ዕለት ኑሮዋቸው በተግባር ሲጠቀሙበትና ወደ ልምድ ሲለውጡ ነው። እዚህ ላይ ለመድረስ ብዙ ጊዜ ይጠይቃል።

እንግዲህ የዲሞክራሲ ዓይነቶች በዚህ ሁኔታ ከተረዳን ዘንዳ በአለው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሕይወታችን ስንገመግመው ያለው ሥርዓት በዲሞክራሲ ሚዛን ምን ዓይነት እንደሆነ መረዳት የሚያዳግተን አይሆንም። ዓይነቶቹን ከተረዳን ዘንዳ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ብናቀርብ ልዩነታቸውን በግልጽ ልንረዳ እንችላለን።

1. ሕዝብ መቼም የማንኛውም ዲሞክራሲ መሠረት ነው። ሁሉም ዓይነት ዲሞክራሲ ሕዝብን ወክሎ ለሕዝቡ አሳቢና ተቆርቋሪ ነኝ በማለት እራሱን ያወድሳል። ሕዝብ ስንል ምን ማለታችን ነው? ምን ያክልና የትኛውን የሕዝብ ክፍል? ያለፈው የደቡብ አፍሪካ መንግሥት ከአራት ሚሊዮን ያነሱ ነጮችን ይዞ ከ26 ሚሊዬን በላይ የሆኑት ሕዝቦችን አግልሎ ስለ ሕዝብ ማውራት ይችላል። በአገራችንም የኢሕአዴግ መንግሥት ሕዝብ ሲል የትኛውን ነው?
2. በሥርዓቱ ውስጥ ውሣኔ ሰጭው ኃይል የትኛው ነው? ይህ በጣም አስፈላጊና ተገቢ ጥያቄ ነው። ዲሞክራሲን ሥርዓት ለመለየት በአገራችን ውስጥ ውሣኝ ኃይል ማነው ብንል ያለጥርጥር ኢሕአዴግ መሆኑን በቀጥታ መመልከት ይቻላል። ሌላው ቀርቶ በሽግግሩ መንግሥት የሚወሡ የዕለት ውሣኔዎችን ብንመለከት ዲሞክራሲያዊ ለማስመሰል ለድምፅ ብልጫ አቶ መለስ ካላበቁት በስተቀር ሁሉንም ውሣኔች በማሰሪያ መልኩ እንደፈለጋቸው የሚዘጉት አቶ መለስ ናቸው። በዚህ ተጨባጭ ማስረጃ ከተፈለገ በምክር ቤት ከሁለት መቶ በላይ የሚሆኑት በኢሕአዴግ ቀርበው ለኢሕአዴግ የተወሡ ናቸው።

3. ሕጋዊነት /Legality / ስንል ምን ማለታችን ነው። በሥርዓቱ ውስጥ ያለውን ሁኔታ መርምሮ «ከዚህ እስከዚህ መንቀሳቀስ ትችላለህ ሕጋዊ መብቶችህ ናቸው» የሚባሉትን ነገሮች በአንክሮ ማጤን ያስፈልጋል። ወደ አገራችን መለስ ከማለታችን በፊት የደቡብ አፍሪካን ሁኔታ በድጋሚ እንመልከት የደቡብ አፍሪካ መንግሥት በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የዘረኛነት ፖሊሲውን በመብት ደረጃ አስቀምጦታል። ይኸውም ጥቁር ከነጭ ጋር በተለያየ ክልል መኖር እንዳለበትና በምንም ዓይነት መቀላቀል እንደማይቻል በዘርና በጉሣ ለይቶ የሚያስቀምጥ ሥርዓት ስለነበር ዘረኝነትን ሕጋዊ መብት ያደርጋል።

4. ሕጋዊነት የሌለው /Illegal / የደ.አፍሪካ ሕገ መንግሥት በአንፃሩ አፓርታይድን /ዘረኝነትን/ የተቃወመን ሁሉ ሕገ ወጥ በማድረግ እርምጃ ሲወስድ ቆይቶአል። ስለዚህም ክቡር ሕዳጣን ነጮች ኔልሰን ማንዴላን በእሥር ቤት ከሃያ ዓመት በላይ ያማቀቁት። ፓርቲያቸውን የአፍሪካ ብሄራዊ ኮንግረስን ነጮቹ ሕገ ወጥ ነው በማለት ለብዙ ዓመታት በጫካ እንዲታገል ያደረጉት። ዛሬ ግን ሕገ ወጥ የተባሉት ሕጋዊ ሆነው ያለፈው ሕጋዊ የተባለው ሥርዓት ወደ ሕገ ወጥነት ተለውጦአል። ስለዚህም ነው እንግዲህ መሬት የመንግሥት ነው ከተባለ መሬትን በግል መያዝ ሕጋዊ አይደለም የሚያሰኘው።

5. አሁን ባለው ሥርዓት ውስጥ ምን ዓይነት ውሣኔችን መወሠን ይቻላል? ለሕዝብ ውሣኔ ደረጃ ሕዝብ ተወያይቶ የሚወሥናቸው ጉዳዮች ምን ዓይነት ናቸው? ለምሣሌ በመሬት ስሪቱና በባለቤትነት ጉዳይ ላይ ሕዝብ ተወያይቶ መሬት ለባለቤቱ መሆን አለበት፣ የመሸጥ መለወጥ መብቱ የተጠበቀ መሆን አለበት ብሎ ቢጠይቅ ይህ መብቱ የተጠበቀ እስካልሆነና በራሱ ጉዳይ ተወያይቶ በሥልጣን የተቀመጠውን ባለሥልጣን ካላስገደደው የሕዝብ ውሣኝነት ምኑ ላይ ነው?

6. ምን ዓይነት ጉዳዮች ናቸው ለሕዝብ ውሣኔ ክፍት የሆኑት? አንድ ሥርዓት ምን ያህል የሕዝብ ተሳትፎን ያካትታል? በምን ዓይነት ሁኔታዎች ላይ ነው ሕብረተሰብ የሚያሳትፈው? እንዴት ይወሥናል? በዚህ ሁኔታ ብዙ ማለት ይቻላል። ዳሩ ግን ጊዜ ስለማይበቃ አንዳንድ የተወሠኑ ጉዳዮችን ለማንሳት እወዳለሁ። የኤርትራ ጥያቄ፣ የትምህርት ፖሊሲ፣ የመሬት የባለቤትነት ጥያቄ፣ ምን ዓይነት መንግሥት፣ የግዛት ክልሎችን በተመለከተ የትኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ይህን ሁሉ ጉዳይ ተወያይቶ ከውሣኔ ያደረሰው ማነው? <u>የውሣኔ ተሳትፎም ሆነ ተወያይቶ መቀበል የዲሞክ. ሲ. ዋነኛ ምሰሶ ነው</u>።

7. ድርጅትን በተመለከተ በምን ዓይነት መልክ መደራጀት ይቻላል? በአገራችን መደራጀት እንደ ዲሞክራሲ መብት ሲወራለት ሶስት ዓመት አስቆጥሮአል። ጥያቄው ግን ከዚህ በፊት እንዳየነው ብዙ ድርጅቶች በአገር ውስጥ መንቀሳቀስ ሲፈቀድላቸው ብዙዎቹ ተከልክለዋል። ፀረ ቻርተር ናቸው በመባል በአገር ውስጥ እንዲደራጁ ከተፈቀደላቸው ብዙ ዎቹ የቻርተሩ ባለቤት በሚስማማው መሠረት ካልሠሩ በፀረ ቻርተርነት ይባረራሉ። አለያ እንቅስቃሴያቸው የተወሠነ ይሆናል። እሥርም የደረሰባቸው ሞልተዋል። ከሙያ ማኅበራት አንፃር የኢትዮጵያ

